# መመሪያ ቁጥር 892/2014

# የሰሊጥ እና ነጭ ቦሎቄ ግብይት አፈጻጸም (ማሻሻያ) የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር መመሪያ

ከሰሊጥ እና ነጭ ቦሎቄ ግብየት ጋር በተያያዘ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመቅረፍ የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ግብይት አፈፃፀም መመሪያን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ደንብ ቁጥር 178/2002 አንቀጽ 27 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1) **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ግብይት አፈጻጸም (ማሻሻያ) መመሪያ ቁጥር 892/2014**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2) **ማሻሻያ**

የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ገብይት መመሪያ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. ከመመሪያው አንቀጽ 6.1.2 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (6.1.3) ተጨምሯል፣

   *(6.1.3)* ማንኛውም የግብይት ተዋናይ አንድ የምርት ዘመን ያላለፈበትም ቢሆንም የሰሊጥ እህል እና የነጭ ቦሎቄ ምርቶችን በማንኛውም መጠንና ጥራት በክምችት ይዞ ማቆየት የሀገሪቱን የወጪ ምርቶች ግብይት የሚያጎድፍ ወይም የሚጎዳ መሆኑን በመግለጽ በሰሊጥ እና ነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 178/2002 እና በሰሊጥ እና ነጭ ቦሎቄ ግብይት አፈጻጸም መመሪያ በተገለጸው መሰረት ለወጪ ገበያ መድረክ አቅርቦ መሸጥ እንዳለበት ሚኒስቴሩ በጽሑፍ ባሳወቀው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተፈጻሚ ማድረግ አለበት፡፡

3) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2(1) ላይ የተመለከተው ድንጋጌ በተላለፈ ማንኛውም የግብይት ተዋናይ ላይ የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 178/2008 ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡

4) **የመመሪያው የተፈፃሚነት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከግንቦት 5 ቀን 2014ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ ግንቦት 5 ቀን 2014ዓ/ም

ገብረ መስቀል ጫላ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር